EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

# የበጀት ዓመት 2024 (FY24) የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ አቅራቢ ስምምነት

ሴፕቴምበር 2023

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች እንኳን በደህና መጣችሁ!



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# የዙም ተሳትፎ

ቀድመው መውጣት ይፈልጋሉ? በማንኛውም ጊዜ **ከስብሰባ ይውጡ** የሚለውን አዝራርን ይጫኑ።

ጥያቄዎችዎን የ Q&A feature (**የጥያቄና መልስ ምርጫን**) በመጠቀም ያስገቡ።





ወደ **መገልገያ ጽሁፎች** የሚወስዱ ተጨማሪ **መረጃዎች** እና **ማስፈንጠሪያዎች** እዚህ ይጋራሉ።

ምርጫዎ በሆነ ቋንቋ ስብሰባውን ያዳምጡ። **የአማርኛ** ወይም **የስፓኒሽ አስተርጓሚን** ለማግኘት እዚህ ይጫኑ።

# በቀጥታ የሚተላለፉ ጥያቄዎች እና መልሶች









ጥያቄዎን እዚህ ይጻፉ እና ያስገቡ የምለውን ይጫኑ።

# የዛሬ ተናጋሪዎች ጋር ተዋወቁ

- **Hannah Matthews**፣ የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE)፣ የቅድመ ትምህርት ክፍል (DEL) ዳይሬክተር፣ ፖሊሲ፣ እቅድ እና ምርምር
- **Sara Mead**፣ የቅድመ ትምህርት ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ፣ ኦፊስ ኦፍ ዚ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን





# አጀንዳ

1. ለFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ የአቅራቢ ስምምነቶች አጠቃላይ እይታ
2. የመታለፍ ሂደት
3. Q&A
4. መዝጊያ እና ቀጣይ ደረጃዎች

# ለFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ የአቅራቢ ስምምነቶች አጠቃላይ እይታ

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ

- በበጀት ዓመት (FY24)፣ OSSE በልጅ ማሳደጊያ ተቋም (CDF) የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር አማካኝነት ለቅድመ አስተማሪዎች ማካካሻን ለመጨመር የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፎችን በቀጥታ ለልጅ ማሳደጊያ ተቋማት ያከፋፍላል።
  - የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ከአሁን በኋላ በAidKit በኩል በቀጥታ ክፍያዎችን አያገኙም።
- ከ CDF የደመወዝ ክፍያ ገንዘብ ቀመር ገንዘቦችን ለመቀበል፣ የልጅ እድገት ተቋማት በOSSE ፈቃድ የተሰጣቸው እና ብቁ ለሆኑ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች፣ በሥራ መደብ እና በዲግሪ፣ በOSSE ለ FY24 የተቋቋመውን ዝቅተኛ ደመወዝ የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደሞዞችን ለመክፈል መስማማት አለባቸው፣

# የFY24 የአቅራቢ ስምምነቶች

- የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ውስጥ ለመሳተፍ፥
  - ድጎማ-የማይወስዱ አቅራቢዎች የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ የአቅራቢ ስምምነትን መሙላት አለባቸው
  - ድጎማ-የሚወስዱ አቅራቢዎች የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ተደማሪ ውሎችን የድጎማ ስምምነታቸው ላይ ጨምረው መሙላት አለባቸው
- የአቅራቢው ስምምነት እና የድጎማ ተደማሪ ውል በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፈንድ ውስጥ ለመሳተፍ ተመሳሳይ መስፈርቶችን ያካትታሉ።
- አቅራቢዎች ሁሉንም የስምምነት ውሎች ወይም ተደማሪ ውሎችን ማክበር አለባቸው።

# ቀነ-ገደቦች

| የFY24 መርጦ የመግባት/ ማመልከቻ እና ስምምነት የማስረከቢያ ቀነ ገደቦች<br>*ሁሉም ቀነ ገደቦች 5 p.m. ላይ ናቸው ET | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሩብ ዓመት | የአቅራቢ መርጦ የመግባት/ ማመልከቻ ቀነ ገደብ | የአቅራቢ ስምምነት ቀነ ገደብ | የDELLT ማሻሻያዎች ቀነ-ገደ | የክፍያ ስርጭት |
| ሩብ አመት አንድ | ሴፕቴምበር 15፣ 2023 | ሴፕቴምበር 30፣ 2023 | ኦክቶበር 31፣ 2023 | ዲሴምበር 2023 |
| ሩብ አመት ሁለት | ዲሴምበር 15፣ 2023 | ዲሴምበር 31፣ 2023 | ጃኗሪ 31፣ 2024 | ማርች 2024 |
| ሩብ አመት ሶስት | ማርች 15፣ 2024 | ማርች 31፣ 2024 | ኤፕሪል 30፣ 2024 | ጁን 2024 |
| ሩብ አመት አራት | ጁን 15፣ 2024 | ጁን 30፣ 2024 | ጁላይ 31፣ 2024 | ሴፕቴምበር 2024፣ 2023 |

የልጅ እድገት ተቋም ለ FY24 አንድ ጊዜ ብቻ ማመልከት እና አንድ ስምምነት መሙላት ይኖርበታል። አንድ የልጅ ማሳደጊያ ተቋም የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ስምምነትን ወይም ተደማሪ ውሎችን ከተፈጸመ በኋላ፣ የፕሮግራሙን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ከቀጠሉ የቀሩትን የFY24 የሩብ አመት የCDF ደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት ክፍያዎችን ወዲያውኑ ያገኛሉ።

# የአቅራቢው ስምምነት ምን ይሸፍናል?

- የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር መግለጫ
- የስሌት እና ክፍያዎች መርሃ ግብር
- የገንዘብ ድጋፎች ከመጠን በላይ እና ከመጠን በታች ክፍያ
- የገንዘብ ድጋፍን መጠቀም
- የአቅራቢ መስፈርቶች፣ የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶችን ጨምሮ
- የበጀት መስፈርቶች
- ዓመታዊ ምልከታዎች
- መዝገቦች፣ የመመርመር እና ቅጂ የማድረግ መብት
- ክትትል እና ኦዲት ማድረግ
- ግብሮች እና ክፍያዎች
- ማካካሻ
- የፈንዶች መገኘት
- የስምምነት ቆይታ
- ስምምነትን ማቋረጥ
- የስምምነትን ማሻሻያ
- አለመግባባትን መፍታት
- መታለፍ/መልቀቅ
- የተከፋይ ተወካይ
- የዲስትሪክት ነዋሪዎችን መቅጠር
- የአለመታዝዝ መፍትሄዎች
- የወጪዎች/ክፍያዎች አለመፈቀድ
- ነባሩን መተካት
- መመደብ
- ፊርማዎች

# የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር

- በFY24፣ የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማቶች ይሰላሉ እና በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ ይከፋፈላሉ።
- ለእያንዳንዱ የልጅ ማሳደጊያ ተቋም የሩብ አመቱ ሽልማት ጠቅላላ የCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር ሽልማት፣ በአራት (4) ሲካፈል ነው።
- በሴፕቴምበር 2023፣ OSSE ለFY24 የCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር ሽልማት ክፍያዎችን እንደሚጨምር አስታውቋል። ተሳታፊ ተቋማት ባሁን ጊዜ እስከ 60 በመቶ የመሠረታዊ ሽልማት እና ልዩ የFY24 ተጨማሪ ማሟያ የሚሆነውን የፍትሃዊነት ማስተካከያ ገንዘብ ያገኛሉ።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **መሰረታዊ ሽልማት**<br><br>አሁን ባሉት ደመወዞች እና በዝቅተኛ ደመወዞች መካከል ያለው ልዩነት በሚና እና በFTE የትምህርት ማስረጃ | + | **አስተዳደራዊ እድገት**<br><br>ከመሰረታዊ ሽልማት 15 በመቶ | + | **የፍትሃዊነት ማስተካከያ**<br><br>እስከ 60 በመቶ የሚሆነው የመሰረታዊ ሽልማት እንደ ፈቃድ እንደተሰጠው አቅም ድርሻ ይወሰናል | + | **የFY24 (የ2024 በጀት ዓመት) ማሟያ**<br><br>30 በመቶ የመሠረት ሽልማት፣ የአስተዳደር ማሻሻያ እና የፍትሃዊነት ማስተካከያ ገንዘብ ድምር | = | የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት |

# የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ማግለጫ፥ የመሠረት ሽልማት ስሌት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የመምህራን ብዛት – CDA | | የደመወዝ ማሟያ መምህር – CDA | | |
| የመምህራን ብዛት– AA | | የደመወዝ ማሟያ መምህር– AA | | |
| የመምህራን ብዛት– BA | ✖ | የደመወዝ ማሟያ መምህር– BA | = | መሰረታዊ ሽልማት |
| የረዳት መምህራን ብዛት – ከ CDA በታች | | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – ከ CDA በታች | | |
| የረዳት መምህራን – CDA | | የደመወዝ ማሟያ ረዳት መምህር – CDA | | |
| የረዳት መምህራን – AA | | የደመወዝ ማሟያ –ረዳት መምህር AA | | |

- መሰረታዊ ሽልማቱ የሚሰላው በአንድ ተቋም ውስጥ ያሉትን የመምህራን ብዛት፣ በሚና እና በትምህርት ማስረጃ ወይም በዲግሪ መሰረት በማድረግ፣ በተጓዳኝ የደመወዝ ማሟያ በማባዛት እና ጠቅላላውን በመደመር ነው።
- የመምህራን ብዛት እና የትምህርት ማስረጃ ደረጃዎች በቅድመ ትምህርት ፈቃድ መስጫ መሳሪያ ክፍል (DELLT) ውስጥ ባለው ተቋም ሪፖርት በተደረገው የሰራተኞች አቅርቦት ውሂብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

# የአስተማሪ የሠራተኛ ዓይነቶች

- ከOSSE የገንዘብ ድጋፎችን የሚያገኙ የልጅ እድገት ተቋማት ብቁ ለሆኑ መሪ መምህራን እና ረዳት አስተማሪዎች በDELLT ውስጥ በሚከተሉት የሰራተኛ አይነቶች፣ ዝቅተኛውን ደመወዝ የሚያሟሉ ወይም ከዚያ የሚበልጡ ደመወዞችን መክፈል አለባቸው።

በDELLT ውስጥ የሚከተሉት የሰራተኞች አይነቶች እንደ ***ረዳት መምህር*** ብቁ ይሆናሉ፡-

- ረዳት አስተማሪ
- ሞንቴሶሪ ረዳት መምህር
- የPre-K የማሻሻያ እና ማስፋፊያ ፕሮግራም (PKEEP) ረዳት መምህር
- ተባባሪ የቤት እንክብካቤ ሰጪዎች

በDELLT ውስጥ የሚከተሉት የሰራተኞች አይነቶች እንደ ***መሪ መምህር*** ብቁ ይሆናሉ፡-

- መምህር
- ሞንቴሶሪ መምህር
- የተስፋፋ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ
- የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪዎች

# የአስተማሪ የትምህርት ማስረጃዎች

- የሚፈለገው ዝቅተኛ ደመወዝ እና ተጓዳኝ የደመወዝ ማሚያ በDELLT ውስጥ በተሰነደው፣ በተገመገመው፣ እና በጸደቀው መሰረት አስተማሪ በሚኖረው ከፍተኛ የትምህርት ማስረጃ ወይም ዲግሪ ላይ የሚመሰረት ይሆናል።
- ለመሪ መምህራን፡-
  - ለ"BA" የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ የቅድመ ልጅነት ትምህርት (ECE) የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በ ECE ውስጥ ከ24 የትምህርት ሰአታት በላይ ወይም እኩል የሆነ የመጀመሪያ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ይኑርዎት።
  - ለ"AA" የደመዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፡ በ ECE ተባባሪ ዲግሪ *ወይም* በECE ከ24 ወይም ከዚያ የሚበልጥ የትምህርት ሰዓታት ያለው ተባባሪ ዲግሪ ይኑርዎት።
  - ለ"CDA" የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ የልጅ እድገት ተባባሪ (CDA) ወይም በECE ውስጥ ከ15 ሰዓታት በላይ ወይም እኩል የሆነ 48 የትምህርት ሰአታት ይኑርዎት።
- ለረዳት መምህራን፥
  - ለ"AA" የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ ተባባሪ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ይኑርዎት።
  - ለ"CDA" የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ CDA ይኑርዎት።
  - ከ "CDA ላነሰ" የደመወዝ ማሚያ ብቁ ለመሆን፣ ከCDA ያነሰ ይኑርዎት።

# የFY24 የደመወዝ ማሟያ

| ሚና | የትምህርት ማስረጃዎች | የFY24 የደመወዝ ማሟያ (አመታዊ) |
|---|---|---|
| ረዳት አስተማሪ | ከ CDA ያነሰ | $2,329 |
| | CDA | $9,470 |
| | ተባባሪ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $12,726 |
| መሪ መምህር | CDA | $8,503 |
| | ተባባሪ ዲግሪ | $18,079 |
| | የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $29,344 |

- የደመወዝ ማሟያ በአማካኝ ደመወዝ እና ለአስተማሪ በሚና እና በትምህርት ማስረጃ መሰረት ለአንድ መምህር በሚሰጠው ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርት መካከል ያለው ልዩነት ነው።
- አማካይ የመምህር ደመወዝ በ2022 የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ ዳሰሳ ጥናት ላይ በተሰጡ ምላሾች ላይ የተመሰረተ ነው።
- ለእያንዳንዱ ሚና የደመወዝ ማሟያ የተወሰነ መጠን ነው።

# አቅራቢዎች በDELLT ውስጥ የሰራተኞች መዝገቦችን ለማዘመን ያላቸው ቀነ-ገደቦች

| የDELLT መዝገቦችን ለማዘመን የFY24 የመጨረሻ ቀነ-ገደቦች | |
|---|---|
| ሩብ ዓመት | የመጨረሻ ቀነ-ገደብ |
| ሩብ አመት አንድ | ኦክቶበር 31, 2023 |
| ሩብ አመት ሁለት | ጃኗሪ 31፣ 2024 |
| ሩብ አመት ሶስት | ኤፕሪል 30, 2024 |
| ሩብ አመት አራት | ጁላይ 31, 2024 |

- የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማቶች በየሩብ ዓመቱ እንደገና ይሰላሉ።
- ሁሉም አስተማሪዎች እና ረዳት አስተማሪዎች በስሌቱ ውስጥ እንዲካተቱ እና ከከፍተኛ የትምህርት ማስረጃቸው ጋር የሚመጣጠን የደመወዝ ማሟያ እንዲመደብላቸው አቅራቢዎች በDELLT ውስጥ ያሉ የሰራተኞች መዝገቦችን ወቅታዊ እና ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
- የሰራተኛ መዝገቦችን ለማዘመን እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ወይም ስለ ትምህርት ሰዓቶች ጥያቄ ያላቸው የተቋም መሪዎች የተመደበላቸውን የፍቃድ ሰጪ ባለሙያ ማነጋገር አለባቸው።
- ማሳሰቢያ፥ የOSSE የፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ውስጥ ተሳትፏቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ፣ ሁሉም የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት በDELLT ውስጥ ወቅታዊ የሰራተኛ መዝገቦችን እንዲይዙ ያዛሉ።

# አስተዳደራዊ እድገት

- የአስተዳደር ማሻሻያው የመሰረታዊ ሽልማት 15 በመቶ ነው።
- ለተቋሙ የግዴታ የደመወዝ ክፍያ ግብሮች እና ሌሎች ሊሆኑ የሚችሉ ተጨማሪ ወጪዎችን ለመጨመር የገንዘብ ድጋፎችን ይሰጣል።

መሰረታዊ ሽልማት ✖ 15 በመቶ = አስተዳደራዊ እድገት

# የፍትሃዊነት ማስተካከያ

- የፍትሃዊነት ገንዘብ ማስተካከያው ከመሰረታዊ ሽልማቱ እስከ 60 በመቶ ይደርሳል፣ ይህም በተቋሙ ድጎማ ምዝገባ ላይ ፈቃድ እንደተሰጠው አቅም ድርሻ ላይ የተመሰረተ ነው።
- ቤተሰቦችን እና አነስተኛ ኢኮኖሚያዊ ሃብቶች ያላቸውን ማህበረሰቦችን ለሚያገለግሉ የልጅ እድገት ተቋማት የተጨመረ የገንዘብ ድጋፍን ይመራል።
- በልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ የማይሳተፉ ተቋማት በመሰረታዊ ሽልማታቸው ላይ ፍትሃዊነት ማስተካከያዎችን አያገኙም።

የድጎማ ምዝገባ ÷ ፈቃድ ያለው አቅም × መሰረታዊ ሽልማት × 60 በመቶ = የፍትሃዊነት ማስተካከያ

በሴፕቴምበር 2023፣ OSSE ለFY24 የCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር ሽልማት ክፍያዎችን እንደሚጨምር አስታውቋል። ተሳታፊ ተቋማት ባሁን ጊዜ እስከ 60 በመቶ የመሠረታዊ ሽልማት እና ልዩ የFY24 ተጨማሪ ማሟያ የሚሆነውን የክፍያ ፍትሃዊነት ገንዘብ ማስተካከያ ያገኛሉ።

# የFY24 (የ2024 በጀት ዓመት) ማሟያ

- OSSE በፕሮግራሙ ትግበራ የመጀመሪያ አመት ላይ ተቋማት ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶችን ለማሟላት እንዲችሉ ለመደገፍ የFY24 ሽልማቶችን እየጨመረ ነው።
- የFY24 ማሟያ የመሠረት ሽልማት፣ የአስተዳደር ማሻሻያ እና የፍትሃዊነት ማስተካከያ ድምር 30 በመቶ ነው።

(መሰረታዊ ሽልማት + አስተዳደራዊ እድገት + የፍትሃዊነት ማስተካከያ) × 30 በመቶ = የFY24 (የ2024 በጀት ዓመት) ማሟያ

# የሠራተኛ ለውጦች

- DELLT እንዲዘመን የተሰጠው የመጨረሻ ቀነ-ገደብ ካለፈ በኃላ፣ በተቋሙ የተቀጠሩ መሪ እና ረዳት አስተማሪዎች ቁጥር፣ ወይም በትምህርት ማስረጃቸው ላይ የሚደረጉ ማንኛውም ለውጦች ላይ በመመስረት OSSE የሩብ ዓመት የክፍያ መጠን ላይ ማስተካከያ አያደርግም።
- ከሩብ ዓመት የመጨረሻ ቀነ ገደብ በኋላ በሠራተኞች ላይ ለውጦች የሚያጋጥሟቸው አቅራቢዎች ለቀጣዩ ሩብ ጊዜ ከመጨረሻ ቀነ ገደብ በፊት የሰራተኞችን መዝገቦች ማዘመን አለባቸው፣ እና በሚቀጥለው ሩብ ክፍያ ላይ የተንፀባረቁ ዝመናዎችን ያያሉ።

# የገንዘብ ድጋፎች ከመጠን በላይ እና ከመጠን በታች ክፍያ

- አቅራቢዎች በተሰላ ክፍያ ላይ ስህተት እንዳለ ካመኑ የክፍያ መግለጫቸው በደረሰው በ30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለOSSE ማሳወቅ አለባቸው።
- የተቋሙ የሩብ ዓመት ክፍያ ከክፍያ መግለጫው የተለየ ከሆነ፣ አቅራቢው የሩብ ዓመት ክፍያውን በተቀበለ በአስር (10) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የስህተት ሪፖርትን ለOSSE ማቅረብ አለበት።
- አቅራቢው መጠኑ ምንም ይሁን ምን ሁሉንም የትርፍ ክፍያዎች ለOSSE ሪፖርት ማድረግ አለበት።
- ለአቅራቢዎች የተከፈለው ትርፍ ክፍያ ከወደፊቱ የሩብ ዓመት ክፍያዎች በመቀነስ ይመለሳል።
- ከመጠን በታች የሆኑ ክፍያዎች በሚከተለው የሩብ ዓመት ክፍያ ላይ ይታከላሉ።

# የገንዘብ ድጋፍን መጠቀም

- የCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር ሽልማቶች ለሚከተሉት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡-
  - ለመሪ እና ረዳት አስተማሪዎች ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶችን ለማሟላት።
  - ለተጨማሪ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እና ሌሎች የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞች የሰራተኞች ደመወዝ ወይም ማካካሻ ለመክፈል።
  - ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እና ሌሎች የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞች የጤና ውጪዎች እና ሌሎች ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞችን ለመክፈል።
  - ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶች እና/ወይም ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የOSSE መስፈርቶችን ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመክፈል።
  - ለህጻናት የእንክብካቤ እና የቅድመ ትምህርት አገልግሎቶችን ከመስጠት ጋር የተያያዘውን የተቋሙ ቀጥተኛ የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለመክፈል።
- ብዙ ፋሲሊቲዎችን የሚያንቀሳቅስ አቅራቢ በፈንዱ ውስጥ ከሌሉ ተቋማት ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ለመሸፈን ገንዘብን መጠቀም አይችልም።

# የሰራተኛ ደመወዝ እና የሰዓት ክፍያዎች

- የመጀመሪያውን የሩብ ዓመት ክፍያ ከተቀበሉ በኋላ፣ አቅራቢዎች ለመምህራን እና ለረዳት መምህራን ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶች፣ በስራ እና በትምህርት ማስረጃ፣ የሚያሟላ ወይም የሚበልጥ ደመወዝን ወይም የሰዓት ክፍያዎችን መክፈል አለባቸው ፡፡

| የሰራተኛ አይነት | የትምህርት ማስረጃዎች | ለFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (አመታዊ ደመወዝ) | ለFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች (የሰአት ደመወዝ) |
|---|---|---|---|
| ረዳት አስተማሪ | ከ CDA ያነሰ | $43,865 | $21.09/ሰዐት |
| | CDA | $51,006 | $24.52/ሰአት |
| | ተባባሪ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $54,262 | $26.09/ሰአት |
| መሪ መምህር | CDA ወይም 48 ክሬዲት ሰአታት በቅድመ ልጅነት ትምህርት (ECE) ከ15 ሰአታት በላይ ወይም እኩል የሆነ | $54,262 | $26.09/ሰአት |
| | በECE ተባባሪ ዲግሪ ወይም በECE ውስጥ 24 ክሬዲት ሰአታት በላይ ወይም እኩል የሆነ ተባባሪ ዲግሪ | $63,838 | $30.69/ሰአት |
| | በ ECE የመጀመሪያ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ወይም በECE የመጀመሪያ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) ከ24 ክሬዲት ሰአታት በላይ ወይም እኩል የሆነ | $75,103 | $36.11/ሰአት |

# የሰራተኛ ደመወዝ እና የሰዓት ክፍያዎች

- አቅራቢዎች በየሰዓቱ በሚከፈላቸው ክፍያ ወይም ዓመታዊ ደመወዝ አማካኝት ለሠራተኞች የሚከፈሉትን ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።
- አቅራቢዎች በየሩብ ዓመቱ የደመወዝ ክፍያ መዝገቦችን በDELLT ላይ ማስገባት አለባቸው።
- አቅራቢው ዝቅተኛውን እና ለመሪ እና ረዳት አስተማሪዎች ከፍተኛውን ደመወዝ የሚገልጽ የደመወዝ መርሃ ግብር መቀበል እና በDELLT ላይ ማስገባት አለበት።
  - አንድ አቅራቢ በOSSE የሚመከረውን የደመወዝ መርሃ ግብር ሊጠቀም ይችላል፣ ነገር ግን ይህን ለማድረግ አይገደድም።
  - የደመወዝ መርሃ ግብሩ ለመሪ እና ለረዳት መምህር በትምህርት ማስረጃ መሰረት ደመወዝ ወይም የሰአት ክፍያን ማካተት አለበት።

# የደመወዝ መርሀ-ግብር ናሙና

| | ደረጃ 1 (ቢያንስ) | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 | ደረጃ 6 | ደረጃ 7 | ደረጃ 8 | ደረጃ 9 | ደረጃ 10 | ደረጃ 11 | ደረጃ 12-15 | ደረጃ 16 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የረዳት መምህር-ትምህርት ደረጃ | | | | | | | | | | | | | |
| ከ CDA ያነሰ | $43,865 | $43,999 | $44,813 | $46,300 | $47,778 | $49,265 | $51,154 | $53,026 | $54,912 | $56,784 | $58,666 | $62,433 | $66,952 |
| CDA | $51,006 | $51,161 | $52,108 | $53,838 | $55,556 | $57,285 | $59,481 | $61,658 | $63,852 | $66,028 | $68,216 | $72,596 | $77,851 |
| ተባባሪ ዲግሪ | $54,262 | $54,427 | $55,434 | $57,274 | $59,102 | $60,941 | $63,278 | $65,594 | $67,927 | $70,242 | $72,570 | $77,230 | $82,820 |
| የመምህር-የትምህርት ደረጃ | | | | | | | | | | | | | |
| CDA | $54,262 | $54,427 | $55,434 | $57,274 | $59,102 | $60,941 | $63,278 | $65,594 | $67,927 | $70,242 | $72,570 | $77,230 | $82,820 |
| ተባባሪ ዲግሪ | $63,838 | $64,031 | $65,216 | $67,381 | $69,532 | $71,696 | $74,445 | $77,169 | $79,914 | $82,638 | $85,377 | $90,859 | $97,436 |
| የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $75,103 | $75,331 | $76,725 | $79,272 | $81,802 | $84,348 | $87,582 | $90,787 | $94,017 | $97,221 | $100,443 | $106,893 | $114,630 |

የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የደመወዝ መርሃ ግብር ናሙናውን ለመቀበል፣ ወይም በተሞክሮ ላይ በመመስረት፣ ለግለሰብ ሰራተኞች በተወሰኑ ደረጃዎች ወይም ባንድ ደረጃዎች ላይ ለመክፈል አይገደዱም። የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የተመከረውን የደመወዝ መርሃ ግብር ለመውሰድ ወይም የራሳቸውን የደመወዝ መርሃ ግብር ለማዘጋጀት ሊመርጡ ይችላሉ፣ ይህም በአመታት ልምድ ላይ በመመስረት ክፍያን ያለያያል፣ በእያንዳንዱ ብቁ ለሆኑ የሰራተኛ ዓይነቶች የሚከፈለው ዝቅተኛ ደመወዝ ለዚያ አስተማሪ ከፍተኛ የትምህርት ማስረጃ ዝቅተኛውን ደመወዝ የሚያሟላ ወይም የሚበልጥ እስከሆነ ድረስ።

# የሥራ ግብዣ ደብዳቤ ወይም ኮንትራት/ውል

- አቅራቢው ለእያንዳንዱ መሪ መምህር እና ረዳት መምህር የሚከተሉትን የሰራተኛ ሁኔታ የሚገልጽ መደበኛ የሥራ ግብዣ ደብዳቤ ወይም ውል መስጠት አለበት፥
  - ስም
  - የሰራተኛ አይነት፥
  - የሥራ ቦታ
  - የሚጠበቁ የሥራ ሰዓታት/የስራ መርሃ ግብር (ተለዋዋጭ መርሃ ግብሮችን ጨምሮ፣ የሚመለከተው ከሆነ)
  - አመታዊ ደመወዝ ወይም የበሰዓት ተመን
  - የሚቀርቡ ጥቅማጥቅሞች
- ኮንትራቱ ወይም ደብዳቤው በሠራተኛው እና በአሠሪው መፈረም አለበት እና በሥራ ውሎች ወይም በማካካሻ ውል ላይ ለውጦችን ተከትሎ መሻሻል አለበት።
- የሰራተኛ ውሉ ወይም የግብዣ ደብዳቤው ቅጂ በሰራተኛው የሰራተኛ መዝገብ ውስጥ በDELLT ላይ መያዝ አለበት።

# የሠራተኛ መዝገቦች

- በፈንዱ ለሚሸፈነው እያንዳንዱ መሪ ወይም ረዳት መምህር፣ ደመወዙ በሙሉ ወይም በከፊል ከCDF የደመወዝ ክፍያ ፈንድ ቀመር የሚከፈለው ሌላ ሰራተኛን ጨምሮ፣ ተቋሙ በDELLT ውስጥ ወቅታዊ የሰራተኞች መዝገቦችን መያዝ አለበት።
- መዝገቦች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፥
  - መሰረታዊ ደመወዝ ወይም ሰዓታዊ ክፍያ፣ በሰዓት ወይም ዓመታዊ ቅርጸት ሊቀርብ የሚችል፣
  - የጤና እና የሌሎች ጥቅማጥቅሞች ፕሮግራሞች ውስጥ መሳተፍ፣
  - የሰራተኛው የግብዣ ደብዳቤ፣ የቅጥር ውል፣ ወይም የሰራተኛውን ደመወዝ ወይም ሰዓታዊ ክፍያ የሚያንፀባርቅ ሌላ ሰነድ፣ እና
  - ፈቃድ ለመውሰድ እንደሚፈለገው የሰራተኞች የትምህርት ምስክር ወረቀቶች።
- እነዚህ መዝገቦች ተገምግመው፣ ተሻሽለው፣ እና በOSSE በ በተደነገገው ቀን (ዎች) በፈቃድ ሰጪ ሰራተኞች እንዲጸድቁ ይላካሉ።

# ምዝገባ፣ የትምህርት ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች

- አቅራቢው ስለ ተቋሙ አጠቃላይ ምዝገባ፣ የተገለገሉ ልጆች ዕድሜ እና የምዝገባ ክፍት የሥራ ቦታ ብዛት ላይ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ያቀርባል።
- አቅራቢው በየአመቱ የትምህርት ክፍያና መርሃ ግብር እና ከፋይ ቤተሰቦች የሚከፈሉ ክፍያዎችን ለOSSE መስጠት አለበት።

# የበጀት መስፈርቶች

- በ1979 በዲስትሪክቱ የሰራተኛ ማካካሻ ህግ መሰረት አቅራቢው ለሁሉም ሰራተኞች የሰራተኛ ካሳ መድን መጠበቅ አለበት።
- አቅራቢው የ2006 የዲስትሪክቱን የኑሮ ደመወዝ ህግ ማክበር አለበት።
  - አቅራቢዎች የ2006 የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የኑሮ ደመወዝ ህግ የማረጋገጫ ቅጽን መፈረም አለባቸው።
  - አቅራቢዎች ይህንን ማረጋገጫ ለOSSE በየአመቱ መስጠት አለባቸው።
- አቅራቢዎች የ2016 የዲስትሪክቱን ሁለንተናዊ የሚከፈልበት ፈቃድ ማሻሻያ ህግን ማክበር አለባቸው።

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ዓመታዊ ምልከታዎች

- አቅራቢዎች OSSE አመታዊ የክፍል ምልከታዎችን እና ግምገማዎችን እንዲያካሂድ መፍቀድ አለባቸው።
- ድጎማ ሰጪዎች በካፒታል ጥራት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው፣ ይህም ይህንን መስፈርት ያሟላል።
- ድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች፡-
  - OSSE የታዛቢ ውጤቶችን ሪፖርት ማድረግ ወይም ማጋራት ወይም ደረጃን ወይም ሌላ የጥራት ስያሜን ለአንድ ተቋም መመደብ የለበትም።
  - OSSE በፕሮግራም ደረጃ የተስተዋሉ የምልከታ ውጤቶችን ከልክ ማሳደጊያ ተቋም ጋር ማጋራት አለበት።
  - OSSE የተመለከቱ የሕፃን ማሳደጊያ ተቋማትን የሚመለከት መረጃን ጨምሮ፣ ልዩ የልጅ ማሳደጊያ ተቋም መረጃን ለይቶ ሳይገልጽ፣ የታዘቡትን የምልከታ ውጤቶች በጥቅል ሪፖርቶች ውስጥ ማካተት አለበት።
  - OSSE የህጻናት ማሳደጊያ ተቋም ማንኛውም የተለየ መረጃ እንዳይገለጽ በሚከለክልበት ወቅት፣ የተመለከቱትን ውጤቶች ለገለልተኛ ተመራማሪዎች ሊያካፍል ይችላል።

OSSE

WE ARE WASHINGTON GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# መዝገቦች፤ የመመርመር እና ቅጂ የማድረግ መብት

- አቅራቢዎች የሁሉንም የሰራተኛ ኮንትራቶች፣ የግብዣ ደብዳቤዎች፣ የደመወዝ መርሃ ግብሮችን እና ለስምምነቱ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ የሌሎች ሰነዶች ቅጂን ከአምስት (5) ዓመታት ላላነሰ ጊዜ፣ ወይም በዚህ ስምምነት ውሎች ወይም አፈጻጸም ምክንያት ወይም ተያያዥነት ያለው ማንኛውም የአስተዳደር ወይም የፍትህ ሂደት የመጨረሻ መደምደሚያ እስኪሰጥ ድረስ ይይዛል፣ ከሁለቱ ረዘም ለሚል ጊዜ።
- OSSE ሁሉንም መዝገቦች የመፈተሽ እና የመቅዳት መብት ይኖረዋል።

# ክትትል እና ኦዲቲ ማድረግ

- አቅራቢዎች መዝገብ መያዝን እና የስምምነቱ ውል መከበራቸውን ለማረጋገጥ ከሁሉም የክትትል እና ኦዲት አካላት ጋር ሙሉ በሙሉ መተባበር አለባቸው።
- ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶችን ለማሟላት አቅራቢዎች በየሩብ ዓመቱ ክትትል ይደረግባቸዋል። OSSE በዚህ የበልግ ወቅት መጨረሻ ላይ በክትትል ሂደት ላይ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል።
- OSSE የሰራተኛ መዝገቦችን ለመገምገም እና የዝቅተኛ ደመወዝ መስፈርቶች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማትን ንኡስ-ክፍል ዓመታዊ ኦዲት ያካሄዳል።
- OSSE በDELLT ውስጥ የተጠቆሙትን በሠራተኛ አወጣጥ ዘይቤዎች ላይ በተፈጠሩ ጉድለቶች ላይ በመመርኮዝ ማንኛውንም የሕጻናት ማሳደጊያ ተቋማትን ኦዲት የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው።

# ግብሮች እና ሌሎች ክፍያዎች

- አቅራቢው በዚህ ስምምነት መሠረት ከተቀበሉት ክፍያዎች ሁሉንም ግብሮች እና ሌሎች ክፍያዎች ለመክፈል ብቻውን ኃላፊነቱን ይወስዳል።
- አቅራቢው ሁሉንም የአሰሪ ግብር የመክፈል እና ለሰራተኞች በሚከፈለው የደመወዝ ክፍያ ላይ ተገቢውን የሰራተኛ ቀረጥ የመክፈል ሃላፊነት አለበት።

# የገንዘብ ማካካሻ እና መገኘት

- በስምምነቱ መሠረት የሚፈለገው ወይም የተከናወነው ማንኛውም ሥራ ጋር በተያያዘ በሠራተኞቹ፣ በተወካዮቹ ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጩ ለሚፈጠረው እርምጃ፣ ጉድለት ወይም ክፍተት ምክንያት በዲስትሪክቱ ላይ በሚደረጉ ማናቸውም ግምገማዎች፣ የገንዘብ ቅጣቶች ወይም ቅጣቶች በተመለከተ፣ አቅራቢው ዲስትሪክቱን እና ወኪሎቹን ይጠብቃል እና ምንም ጉዳት የሌላቸው አድርጎ ይይዛል።
- በስምምነቱ መሠረት የዲስትሪክቱ የፋይናንስ ግዴታዎችን የመወጣት ግዴታ በዲሲ ካውንስል በተፈቀደው መሠረት የተመጣጣኝ ገንዘቦች መገኘት ላይ የተመሰረተ ነው እና በተዛማጅ ሕጎች ተገዢ ናቸው።

# የስምምነት ቆይታ

- ስምምነቱ በOSSE የቅድመ ትምህርት ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ እስከ ሴፕቴምበር 30፣ 2024 ድረስ ተግባራዊ ይሆናል።
- በOSSE ለአቅራቢው የጽሁፍ ማስታወቂያ እስከተሰጠ ድረስ ስምምነቱ በየአመቱ ሊራዘም ይችላል።
- ስምምነቱ ከመጀመሪያው ቀን ጊዜ ጀምሮ ከአራት ጊዜ በላይ ሊራዘም አይችልም።

# ስምምነቱን ማቋረጥ

| የFY24 የመርጦ-የመውጣት የመጨረሻ ቀነ-ገደቦች | |
|---|---|
| ሩብ ዓመት | የመጨረሻ ቀነ-ገደብ |
| ሩብ አመት አንድ | ኦክቶበር 15, 2023 |
| ሩብ አመት ሁለት | ጃኗሪ 15፣ 2024 |
| ሩብ አመት ሶስት | ኤፕሪል 15, 2024 |
| ሩብ አመት አራት | ጁላይ 15, 2024 |

- አቅራቢው በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩይቲ ፈንድ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ማቆም ከፈለገ፣ አቅራቢው ይህንን ስምምነት ለማቋረጥ ካሰበበት ሩብ ዓመት የመጀመሪያው ወር ከ15ኛው ቀን በፊት ለOSSE ሪፖርት ማድረግ አለበት።
  - ያለፉ ከመጠን በታች ክፍያዎችን ለማረም ተገቢ ካልሆነ በስተቀር አቅራቢዎች ውል ከተቋረጠበት ቀን በኋላ ተጨማሪ ክፍያዎችን አያገኙም።
- ገንዘቦችን የተቀበሉ እና በኋላ ከፕሮግራሙ መርጠው የወጡ አቅራቢዎች እስከሚቀጥለው ሩብ ዓመት መጀመሪያ ድረስ ብቁ ለሆኑ ሠራተኞች ቢያንስ የሚፈለገውን ዝቅተኛ ደመወዝ መክፈልን መቀጠል አለባቸው።
  - ለምሳሌ፣ በዲሴምበር ወር ለሩብ ዓመት አንድ ገንዘብ የሚቀበል እና በጃንዋሪ መርጦ ለመውጣት የወሰነ ተቋም እስከ ሙሉ ማርች 2024 ድረስ ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶች ማሟላት አለበት።
- ዲስትሪክቱ የጽሁፍ ማስታወቂያ ሲደርሰው ተፈጻሚ የሚሆን በማንኛውም ምክንያት ይህንን ስምምነት ሊያቋርጥ ይችላል። ዲስትሪክቱ የተቋረጠበትን ምክንያት እና የተቋረጠበትን ቀን የሚገልጽ የማቋረጡ የጽሁፍ ማስታወቂያን ለአቅራቢው ይሰጣል።

# የስምምነትን ማሻሻያ

- ስምምነቱ ሊሻሻል፣ ሊታደስ ወይም ሊራዘም የሚችለው በጽሁፍ ብቻ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖች በስምምነቱ ላይ ማሻሻያዎቹ ላይ መፈረም እና ቀን መጻፍ አለባቸው።
- በዲሲ ካውንስል እርምጃዎች ላይ በመመስረት OSSE የሽልማት ክፍያዎችን ማሻሻል ካስፈለገው፣ OSSE በአንድ ወገን ስምምነቱን ያስተካክላል።
- የገንዘብ ድጎማ በሚቀንስበት ጊዜ፣ OSSE ዝቅተኛው የደመወዝ መስፈርቶች ላይ የተደረገው ማስተካከልን በተመለከተ ለህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት መመሪያ ይሰጣል።

# አለመግባባቶችን መፍታት፣ መታለፍ/መልቀቅ እና የውክልና ተከፋይ

- **አለመግባባቶችን መፍታት፥** አቅራቢዎች/OSSE በስምምነቱ ምክንያት የሚነሱ ማናቸውንም አለመግባባቶችን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለመፍታት መሞከር አለባቸው። ይህ የማይቻል ከሆነ፣ አቅራቢዎች የአለመግባባት መግለጫዎችን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ። OSSE ገምግሞ ለመፍታት ይሞክራል። አቅራቢው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ከጠየቀ፣ የስቴት የበላይ ተቆጣጣሪ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።
- **መታለፍ/መልቀቅ፥** ዲስትሪክቱ በስምምነቱ አፈጻጸም ምክንያት በሰው ወይም በንብረት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት፣ የይገባኛል ጥያቄ ወይም ኪሳራ ተጠያቂ አይሆንም።
- **የውክልና ተከፋይ፥** አቅመ ማጣት ወይም ሞት ሲያጋጥም ለተፈቀደለት አቅራቢ የሚከፈለውን ማንኛውንም ያልተከፈለ ክፍያ እንዲቀበል አቅራቢው ተወካይን መሰየም አለበት።

# የዲስትሪክት ነዋሪዎችን መቅጠር

- ማንኛውም አዲስ የተፈጠሩ የሰራተኛ የስራ መደቦች የዲስትሪክት የመጀመሪያ ምንጭ ህግን ማክበር አለባቸው፣ ይህም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ኗሪዎች ለመፈፀም በውል ምክንያት ከተፈጠሩት ሁሉም አዳዲስ ስራዎች 51 በመቶውን ይፈልጋል።
- ይህ መደበኛ የዲስትሪክት ኮንትራት ቋንቋ ነው፣ እሱም በህጻን እንክብካቤ ድጎማ የአቅራቢ ስምምነት ውስጥም ተካትቷል።
- መስፈርቱ ነባር ሰራተኞችን አይመለከትም እና ተቋሙ በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩይቲ ፈንድ ውስጥ ከመሳተፉ በፊት በነበሩ የስራ መደቦች ላይ ክፍት የስራ መደቦችን መሙላትን አይመለከትም።
- በአጠቃላይ፣ OSSE የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩይቲ ፈንድ የአቅራቢ ስምምነትን በማክበር ምክንያት የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት አዳዲስ ሰራተኞችን ይቀጥራሉ ብሎ አይጠብቅም።

# አለመታዘዝ የሚያስከትሏቸው ነገሮች

- OSSE ሁሉንም የስነምግባር ጉድለት እና አለመታዘዝን ይመረምራል።
- ያለመታዘዝ ማስታወቂያ የደረሳቸው አቅራቢዎች ጉዳዩን ለማስተካከል እድል አላቸው። አቅራቢዎች ያለመታዘዝ ውሳኔን ይግባኝ ማለት ይችላሉ።
- ሁለት ጊዜ ያለመታዘዝ ድርጊት ፈፀምን ተከትሎ፣ አንድ አቅራቢ በMy Child Care DC ላይ በይፋ ተለይቶ ሊወጣ ይችላል።
- ከሦስት የጥሰት ድርጊት በኋላ፣ አንድ አቅራቢ በትንሹ ለአንድ ዓመት ከፕሮግራሙ ሊቋረጥ ይችላል። አቅራቢዎች የመቋረጡ ውሳኔን ይግባኝ ማለት ይችላሉ።
- አለማክበር እና የመቋረጥ ይግባኞች በOSSE መገምገም አለባቸው። ሁሉም የግምገማ ውሳኔዎች የመጨረሻ ናቸው።

# አለመታዘዝ የሚያስከተሏቸው ነገሮች፣ የቀጠለ..

- አቅራቢ ስምምነቱን ካላከበረ፣ OSSE የሚከተሉትን ሊያደርግ ይችላል፥
  - ለጊዜው ክፍያዎችን መያዝ፤
  - የአሁኑን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማገድ ወይም ማቋረጥ፤
  - የአማራጭ ልምምድ አመታት የሉም ወይም በOSSE ውሳኔ ማደስ የለም፤
  - በኦዲት ግኝት ፣ በምርመራ ግኝቶች ፣ በዘገየ መቋረጥ ወይም በስሌት ስህተቶች ላይ በመመስረት ማንኛውንም ትርፍ ክፍያ መሰብሰብ ፤ እና
  - በህጋዊ መንገድ ሊገኙ የሚችሉ ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ።
- የተጭበረበሩ ሰነዶችን፣ መረጃዎችን ወይም ውሂቦችን በማቅረቡ ምክንያት ገንዘብ የሚያገኝ ማንኛውም አቅራቢ ገንዘቡን ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት መልሶ እንዲከፍል ይጠበቅበታል።
- የአቅራቢውን ስምምነት መስፈርቶች መጣሱ የተረጋገጠ ማንኛውም አገልግሎት አቅራቢ ለተጨማሪ እርምጃ ወደ OSSE/DEL ፈቃድ ሰጪ እና ተገዢነት ክፍል ወይም ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ ሊላክ ይችላል።

# የወጪ/ክፍያዎች አለመፈቀድ

- OSSE የሚከተሉትን ሁኔታ የሚያሟሉትን ማንኛውም ወጪዎች ወይም ክፍያዎች ይከለክላል፥
  - OSSE ስምምነቱን በማክበር ወጪ አልተደረጉም ብሎ የወሰናቸው።
  - OSSE በአገልግሎት አቅራቢው ተገቢውን ሰነድ ማቆየት እና/ወይም ማቅረብ ባለመቻሉ ምክንያት በስምምነቱ መሠረት ወጪ መደረጉን ማረጋገጥ አልቻለም።
- አቅራቢዎች ሁሉንም ያልተፈቀዱ ወጪዎችን ወይም ክፍያዎችን የመመለስ ግዴታ አለባቸው።

# መተካት፣ መመደብ እና ፊርማዎች

- ስምምነቱ የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩይቲ ፈንድ በተመለከተ በአገልግሎት አቅራቢው እና በዲስትሪክቱ መካከል የተደረጉ ማናቸውንም ነባር ስምምነቶችን ይተካል።
- ተዋዋይ ወገኖች ይህንን ስምምነት ወይም የዚህን ስምምነት ማንኛውንም መብት ወይም ግዴታ፣ በሕግ አሰራር ወይም በሌላ መንገድ፣ መስጠት ወይም ማስተላለፍ አይችሉም።
- ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ እንዲፈፀም በOSSE እና በልጅ ማሳደጊያ ተቋም መፈረም አለበት።

# የመታለፍ ሂደት

# የመታለፍ ሂደት


- OSSE ለሁሉም ብቁ የሆኑ ሰራተኞች ዝቅተኛውን ደሞዝ ማሟላት ለማይችሉ የህጻናት ማሳደጊያ ተቋማት በFY24 የመታለፍ ሂደትን ያቀርባል።
- በዚህ በልግ መጨረሻ ላይ፣ OSSE ከልጆች ማሳደጊያ ተቋማት ጋር ለመታለፍ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል፣ ለመታለፍ እጩ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ልዩ መመዘኛዎች እና ለመታለፍ ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮግራሞች ማክበር ያለባቸው መስፈርቶችን በተመለከተ መረጃን ያካፍላል።

# የመታለፍ ሂደት

- መታለፍን የሚጠይቁ ተቋማት ዘላቂነት በሌለው የበጀት ጉድለት ሳይሰሩ ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርት ማሟላት አለመቻላቸውን፣ ከሌሎች መስፈርቶች መካከል፣ ለመመዝገብ የፋይናንስ መረጃቸውን ከOSSE ጋር መጋራት ይጠበቅባቸዋል።
- መታለፍ የተፈቀዳለቸው ተቋማት የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት ፈንድ ገንዘብን ለብቁ አስተማሪዎች ደመወዝ ለመጨመር መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፣ የFY24 ዝቅተኛውን ደመወዝ ለማሟላት በበቂ ሁኔታ መጨመር ባይችሉም እንኳን።

# እባኮትን የዛሬውን ክፍለ ጊዜ በምን ቋንቋ እንደተሳተፉ ይንገሩን።

እባክዎ በማያ ላይ ለዙም ምርጫ ምላሽ ይስጡ



# Q&A

# የዛሬውን የመረጃ ክፍለ-ጊዜ ስለተካፈሉ እናመሰግናለን!

በ FY24 የቅድመ ልጅነት ትምህርት ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን የሚከተለውን ይጎብኙ፡- osse.dc.gov/fy24ecepayequity

የመገልገያ ጽሁፎች፥

- ለልጅ እድገት ተቋም መሪዎች FAQ
- የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩይቲ ፈንድ የአቅራቢ ስምምነት (ድጎማ-ለማይወስዱ አቅራቢዎች) ናሙና
- የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ እኩይቲ ፈንድ የአቅራቢ ስምምነት ተደማሪ ውሎች (ድጎማ-ለሚወስዱ አቅራቢዎች) ናሙና

ጥያቄዎች?

- OSSE.ECEPayEquity@dc.gov

EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR